አራምባና ቆቦ!

ኢብሳ ነመራ

በሥራ ላይ ከዋለ ሶስት ወራት ሊሞላው ቀናት የቀሩትን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያስፈጽመው ኮማንድ ፖስት በመጀመሪያው ዙር በህገወጥ ድርጊት ጠርጥሮ በቁጥጥር ካዋላቸው 11 ሺህ 6 መቶ ሰዎች መካከል 9 ሺህ 8 መቶዎችን ወደየቤታቸው ማሰናበቱ ይታወሳል። ኮማንድ ፖስቱ ሰዎቹን የለቀቀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ መሰረት የተሃድሶ ስልጠና ሰጥቶ ነው። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መመሪያ ቁጥር 1 ክፍል ሶስት አንቀጽ 31 “ በህግ መሰረት በኮማንድ ፖስቱ የሚደረግ የተሃድሶ እርምጃዎች” በሚል ርዕስ ስር የሚከተለው ተደንግጓል።

በሕግ መሠረት በኮማንድ ፖስቱ የሚደረግ የተሃድሶ ዕርምጃዎች

1. ለፍርድ መቅረብ ያለበትን ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያደርጋል

2. ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ በተፈጸሙ ሁከትና የብጥብጥ እንቅስቃሴዎች ላይ በቡድን ወይም በግል የተሳተፈና

ሀ) የጦር መሣሪያ ወይም ማንኛውንም የግልም ሆነ የመንግሥት ንብረት የዘረፈና በአቅራቢያው ለሚገኝ የሕግ አስከባሪ ኃይል የዘረፈውን መሣሪያና ንብረት ይህ መመርያ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ በአሥር ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ላለ ፖሊስ ጣቢያ የመለሰና እጁን የሰጠ ሰው፣

ለ) ከዚህ በፊት ለሕገወጥ ተግባራት የገንዘብና ቁሳቁስ ድጋፍ ያደረገና ይህ መመሪያ በወጣ በአሥር ቀናት ውስጥ ለፖሊስ ጣቢያ እጁን የሰጠ ሰው፣

ሐ) ወረቀት በመበተን ፣ አድማ በማድረግ የተሳተፈ፣ ያነሳሳ ሰው ይህ መመርያ በወጣ አሥር ቀናት ውስጥ ለፖሊስ ጣቢያ እጁን የሰጠ ሰው፣

መ) ሰው የገደለ፣ ማንኛውንም ንብረት ያቃጠለ፤ ማንኛውንም ወንጀል የፈጸመ ይህ መመሪያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአሥር ቀናት ውስጥ ለፖሊስ ጣቢያ እጁን የሰጠ ሰው፤ እንደየወንጀል ተሳትፎው ቀላልና ከባድነት፤ ዋና ፈጻሚና አባሪ ተባባሪ መሆኑ ታይቶ በኮማንድ ፖስቱ የተሃድሶ ትምህርት ተሰጥቶት እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

በዚህ መመሪያ መሰረት በተሃድሶ ስልጠና ከተለቀቁት ባሻገር 2 ሺህ 2 መቶ ያህል ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዲታይ ክስ እንዲመሰረትባቸው ተወስኗል።

ይህ ሁኔታ ሰሞኑን በተሃድሶ ስልጠና እንዲለቀቁ የተደረጉና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዲታይ የተደረጉ ሰዎች ላይ የተላላፈው ውሳኔ ሁኔታዎች የወለዱት ድንገተኛ ሳይሆን ሰዎቹ በቁጥጥር ስር ከመዋላቸው በፊት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በጸደቀ የአስቸኳይ ጊዜ መመሪያ መሰረት የተከናወነ ነው። ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ስር የዋሉትም የተለቀቁትም፤ የተወሰኑት ደግሞ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዲታይ የተወሰነባቸው በህግ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በተሃድሶ ወደቤታቸው የተሰናበቱ ሰዎች በቁጥጥር ስር በቆዩባቸው ሁለት ወራት ገደማ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። ከአጀንዳዎቹ መካከል፤ በፍፁም አይደገምም፤ የቀለም አብዮት፤ የኢትዮጲያ ህገመንግስት፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዳሴ የሚሉት ቀዳሚዎቹ ናቸው።

በጦላይ ተሃድሶ ማዕከል ከነበሩት 5 ሺህ 600 ሰዎች መካከል 4 ሺህ 35 ያህሉ የተሃደሶ ስልጠናቸውን አጠናቅቀው በተሰናበቱበት ስነስርአት ላይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ እና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ርዕስ መስተዳድር አቶ ለማ መገርሳ ተገኘተው ነበር። በሌሎቹም የተሃደሶ ማዕከላት የክልልና የፌደራል መንግስት ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች ተገኝተው ነበር። ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች በስነስርአቶቹ ላይ መገኘታቸው መንግስት ለጉዳዩ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል። በየማዕከላቱ የተገኙት የመንግስት ሃላፊዎች “አይደገምም” በሚል መሪ ሃሳብ የተከናወነው የተሃድሶ ስልጠና ወስደው ለተሰናበቱተ ንግግር አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በንግግራቸው ሰልጣኞች ወደ መደበኛ ህይወታቸው እንዲመለሱ መንግሥት ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል። ሠራተኞች የነበሩ ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ፤ ተማሪዎች ደግሞ ትምህርታቸው እንዲቀጥሉ እንደሚደረግም ገልጸዋል። ሥራ አጥ የሆኑ ወጣቶችም በራሳቸው መንገድ ሥራ እንዲፈጥሩ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል። ሠላም፤ ልማትና ዴሞክራሲ የማይነጣጡ የአንድ አገር ህልውና መሰረት መሆናቸውን ወጣቱ ተገንዝቦ እነዚህን እሴቶች የመጠበቅ ኃላፊነቱን እንዲወጣ የጠየቁት ጠቅላይ ምኒስትሩ፤ በተለይ በሁከቱ ውስጥ ከፍተኛ ተሳተፎ የነበረው ወጣቱ ጥያቄ ቢኖረው እንኳን ሕገመንግሥቱ በሚፈቅደው መሰረት የማቅረብና መልስ የማግኘት መብት እንዳለው፤ ይህን ህገመንግስታዊ መብቱን ብቻ እንዲጠቀም አሳስበዋል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንዳይደገም መንግሥትም የራሱን ስህተት ለማረም ጥልቅ ተሃድሶ እያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ወጣቱም የራሱን ስህተት በማረም ከመንግሥት ጋር በመሆን ሠላሙን እንዲጠብቅ መልዕክት አስተላልፈዋል።

መንግስት ባለማወቅ አውዳሚ በነበረው ሁከት ውስጥ ገብተው የራሳቸውንና የወገናቸውን ንበረት እንዲወድም፤ ህይወት እንዲጠፋ የማድረግ ተሳትፏቸው ስህተት መሆኑን ለተገነዘቡና ከህግ በታች ለመሆን ፍቃደኛ ሆነው ህዝቡን ይቅርታ ለጠየቁ ዜጎች ዳግም በህገወጥ ሁከት ውስጥ ከመሳተፍ ራሳቸውን እንዲቆጥቡ፤ ህገመንግስታዊ፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብትና ነጻነታቸውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ፤ እንዲሁም የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ እንዲያስታውሱ ማድረግ የሚያስችል የተሃድሶ ስልጠና መሰጠቱ ለህዝቡ ያለውን ክብርና ለዜጎቹ ደህንነት የሚሰጠውን የላቀ ቦታ ያሳያል።

የተሃድሶ ስልጠና ወስደው በነጻ የተሰናበቱት ዜጎች፣ ዳግም ሆነ ተብሎ በሚነዛ ውዝንብር ተደናግረው ሁከት ውስጥ ላለመግባት፣ ኢትዮጵያን ዳግም ሃገር መሆን በማትችልበት ሁኔታ በእርስ በርስ ግጭት እንድትበተን ለማደረግ ስትራቴጂ ቀርጸው ለሚንቀሳቀሱ ሃገራትና ቡደኖች መናጀ ላለመሆን ቃል ገብተዋል፤ “አይደገምም” በማለት።

በሁከቱ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ዜጎች በተሃድሶ ስልጠና በነጻ ወደተለመደው ህይወታቸው እንዲመለሱ መደረጉን ተከትሎ የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም (ቪኦኤ) በአገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም ጠይቆ ነበር። ለቪኦኤ አስተያየታቸውን የሰጡት የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፤ የኦሮሞ ፌደራላዊ ፓርቲ (ኦፌኮ) እና የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች ናቸው። አመራሮቹ ከሰጧቸው አስተያየቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን እንመልከት።

የመኢአድ ዋና ጸሃፊ አቶ አዳነ ጥላሁን በተሃድሶ የተለቀቁትን ዜጎች አስመልክተው በሰጡት አስተያየት “መጀመሪያውኑም መታሰር አልነበረባቸውም። መሳሪያ ሳይዙ የመብት ጥያቄ ስላነሱ ነው የታሰሩት” ብለዋል። የኦፌኮ ምክትል ሊቀመንበር አቶ ሙላቱ ገመቹም ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል። አቶ ሙላቱ “ እጅ በማንሳት ለቀረበ ሰላማዊ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ የኃይል እርምጃ ነው” ብለዋል።

ይህን የአቶ አዳነን እና የአቶ ሙላቱን አስተያያት የሰማ ኢትዮጵያዊ ሰዎቹ ባለፈው ዓመት ሁከት በተቀሰቀሰበት ወቅት በአገር ውስጥ ያልነበሩና ስለሁከቱ ምንም ያልሰሙ ሊመስለው ይችላል። ምክንያቱም ባለፈው ዓመት ተቀስቅሶ የነበረው የመብት ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ብቻ የቀረበ ባለመሆኑ፤

እርግጥ ነው፤ ባለፈው ዓመት ድንገት ገንፍሎ የወጣው ተቃውሞ ታምቆ የበሰለ ቅሬታ ውጤት መሆኑ አይካድም። በመልካም አስተዳደርና በፍትህ እጦት ተማርረው አቤት የሚሉበት ሰሚ ያጡ ዜጎች፤ የተጀመሩ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶች ተጠናቅቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ወይ ግንባታቸው ቆሟል ተብሎ ቁርጡ የማይታወቅ ላም አለኝ በሰማይ ሆነው ያንገሸገሻቸውና ይህ ሁኔታ እንዲለወጥ አጥብቀው የተመኙ፤ ጥቂቶች ምንጩ ባልታወቀ ሃብት በአጭር ግዜ ውስጥ የአገር በቀል ባለሃብትነት ካባ በሚደፉባቸው ከተሞች ለእለት ጉርስ እንኳን የሚሆን ስራ አጥተው የበይ ተመልካኝ የሆኑ የተማሩና የሰለጠኑ ወጣቶች ላይ የተፈጠረው መከፋትና ተስፋ መቁረጥ ተባብሶ የተቀሰቀሰ ህዝባዊ ተቃውሞ ነው።

ይሁን እንጂ፤ ህዝቡ  ውስጡን ያነፈረውን ቅሬታ አውዳሚ በሆነ መንገድ፤ የራሱንና የሰላም አስከባሪ ኃይል አባላትን ህይወት በሚያጠፋና አካል በሚያጎድል አኳኋን፤ የተገኘውንም የስራ እድልና ማህበራዊ ልማት በሚያጠፋ፤ የልማት ተቋማትንና ፋሲሊቲዎችን በሚያወድም አኳኋን እንዲገለጽ የማድረግ ፍላጎት አልነበረውም። አደባባይ መውጣት ቢያስፈልገው እንኳን የመግደልና የመሞት፤ ራሱ የሚጠቀመበትን ሃብት የማውደም ፍላጎት አልነበረውም። ሊኖረውም አይችልም። የሰው ህይወት ከጠፋና ንብረት ከወደመ በኋላ በየአካባባው ከህብረተሰቡ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ላይ ህዝቡ ያነሳቸው ሃሳቦች ለዚህ አስረጂነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ቅሬታዎች የወለዱት የህዝቡ ተቃውሞ ወደ ሁከትነት የተለወጠው አገሪቱ እንድትተራመስና እንድትፈርስ፤ ራሷን ችላ የማትቆም ደካማ እንድትሆን በሚፈልጉና ይህን እውን ለማድረግ በሚሰሩ የኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ ጠላቶች፤ እንዲሁም በእነርሱ ላይ በተለጠፉ አሁን በአገሪቱ ያለው ዴሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ላይ የተመሰረተው ህገመንግስታዊ ስርአት የሚጎረብጣቸው ትምክህተኛና ጠባብ ብሄረተኛ ቡደኖች ነው። ከሁከቱ ጀርባ የነበሩትን ጃዋር መሃመድ የሚመራውን ኦሮሞ ሚዲያ ኔትና ፌስ ቡክ፤ የኤርትራ መንግስት በሚሰጠው ገንዘብና የፕሮፓጋንዳ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሰውን ኢሳት፤ እንዲሁም መረጃ ዶት ኮም እና መሰል ማህበራዊ ሚዲያዎች ሲያሰራጩት የነበረውን መልዕክት ማስታወስ ለዚህ በቂ አስረጂ ነው። እነዚህ ሚዲያዎች በተለይ ማህበራዊ ሚዲያዎች አሁንም ከዚህ ድርጊታቸው አልተቆጠቡም።

በእነዚህ አካላት መሪነት የተካሄደው በሃይል ህገመንግስታዊ ስርአቱን የማስወገድ ቅስቀሳ ወጣቶችን በማደናገር በስሜታዊነት የራሳቸውንና የሌሎችን ህይወት ለአደጋ የሚያጋልጥ ህገወጥ የሃይል ተቃውሞ ውስጥ እንዲገቡ ገፋፍቷል። የግለሰቦችን ንብረት፤ መኖሪያ ቤት፤ የጤናና የትምህርት ተቋማት፤ የንጹህ መጠጥ ውሃ ማሰራጫ ተቋማት ወዘተ. ወድመዋል። በጃዋርና በኤርትራ በሚመሩት ኢሳትና መረጃ ዶት ኮም ውዥንብር የተደናገሩት ወጣቶች የክልልና የፌደራል የጸጥታ አስከባሪ ሃይል፤ እንዲሁም የአካባቢ ሚሊሻ አባላትን መሳሪያ ለመንጠቅ ግብግብ ይገጥሙ ነበር። መሳሪያ ታጥቀው ተኩስ በመክፈት በጸጥታ አስከባሪዎች ላይ ጥቃት የተሰነዘረበትም አጋጣሚ ነበረ። በተለይ ይህ ሁኔታ ባለፈው ዓመት ማገባደጃና በያዘነው ዓመት መግቢያ ላይ ተባብሶ የአገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ ጥሎ ነበር።

ይህ ሰላማዊ ተቃውሞ አልነበረም። የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ያስፈለገው ይህን የሃገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ የጣለ ሁኔታ በመቀልበስ ሰላምን ለመመለስ ነው። በአስቸኳይ ግዜ አዋጁ መመሪያ መሰረት የደፈረሰውን ሰላም ለመመለስ፣ ባለማወቅ ተደናግረው ሁከት ውስጥ የገቡትንም ሆነ ሆን ብለው ውጤቱን እያወቁ የገቡበትን ከተለመደው ህግን የማስከበር ስርአት በተለየ ሁኔታ በቁጥጥር ስር መዋል አስፈላጊ ነበር።

አሁን በተሃድሶ የተለቀቁት ሰዎቸ የተያዙት በዚህ አኳኋን ነው። እናም ተቃውሞው ሰላማዊ ነበር፣ የተለቀቁት ሰዎች ቀድሞውኑም መያዝ የለባቸውም ነበር የሚለው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች አስተያየት ምክንያታዊ ያለሆነ ከንቱ ነው።

ሌላው በዚህ ጽሁፍ ልመለከተው የምፈለገው አስተያየት፤ የሶስቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች የሚጋሩትን አስተያየት ነው። ይህም የህዝቡ ጥያቄ የፖሊሲ ለውጥ፤ የስርአት ለውጥ ጥያቄ ነው። ስለዚህ የፖሊሲ እና/ወይም የስርአት ለውጥ ነው የሚያስፈልገው የሚል ነው።

ይህ አስተያየት ፍጹም ከእውነታው ያፈነገጠ ነው። በቅድሚያ እጅግ አብላጫ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ቀደም ሲል የጠቀስነው ያቆሰለው ቅሬታ ቢኖርበትም፤ የፖሊሲ ለውጥ ጥያቄ አላቀረበም። የመኢአዱ አቶ አዳነ እና የኦፌኮው አቶ ሙላቱ ገመቹ የትኛውን ፖሊሲ ወይም ስርአት እንዲለወጥ እንደሚፈልጉ ባይገልጹም፤ የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አቶ የሺዋስ የህዝቡ ጥያቄ በዘር ላይ የተመሰረተው ፌደራላዊ መዋቅርና የመሬት ፖሊሲ ይለወጥ የሚል ጥያቄ ቀርቦ እንደነበረ ነው ለቪኦኤ የገለጹት፤

አቶ የሺዋስ በዘር ላይ የተመሰረተ ፈደራሊዝም የመሬት ፖሊሲ እንዲቀየር ጥያቄ ቀርቧል፤ በሚል ያነሱት የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን ውሸትም ነው። ይህ አጀንዳ በተለይ ውጭ አገር በሚኖሩ ትምክህተኞች ተነስቶ ሊሆን ይችላል። አቶ የሺዋስ የህዝብ ጥያቄ ብለው ያቀረቡት ይህ ጉዳይ፤ አብረዋቸው አስተያየት የሰጡት የኦፌኮው ምክትል ሊቀመንበር አቶ ሙላቱ ገመቹና ከ60 በላይ የሚሆኑ በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የማይደግፉት መሆኑን እንኳን ማስተዋል አልቻሉም። ከባለፈው ዓመት ጀምሮ እስከያዝነው ዓመት መግቢያ የነበረው ተቃውሞ መነሻው ይህ የፖሊሲና የስርአት ጥያቄ የቀረበበት ነበር የሚለው አስተያየት ከቅዠት የሚቆጠር ነው። እርግጥ በዋነኝነት በብሄር ላይ የተመሰረተው ፌደራላዊ ስርአት ፈርሶ፤ የብሄር ብዝሃነት የተጨፈለቀበት፤ የህዝብ ሳይሆን የወሰን አንድነት ያላት አገር እንድትመሰረት የሚመኙ ጥቂት ትምክህተኛ ብሄረተኞች መኖራቸው አይካድም። የእነዚህ ጥቂቶች ምኞት ግን እንደ ህዝብ ጥያቄ ተደርጎ ሊቀርብ የሚችል አይደለም።

ከዚህ በተረፈ ህዝብ የፖሊሲ ለውጥ ያስፈልጋል ብሎ ቢያምን እንኳን፤ በሃይል ስርአት መለወጥ አያስፈልገውም። የሚፈልገውን ፖሊሲ ለሚያራምድ አካል ስልጣን በውክልና የመስጠት ህገመንግስታዊ ስርአት አለ። በህገመንግስቱ በተረጋገጠው የፈቀዱትን አቋምና አመለካከት የማራመድ፤ በአቋምና በአመለካከት የመደራጀትና ለፖለቲካ ስልጣን የመወዳደር መብት በግልና በድርጅት ለምርጫ ከሚቀርቡለት ፖሊሲዎች መካከል ይበጀኛል የሚለውን መርጦ ስልጣን በውክልና መስጠት ይችላል። ለምሳሌ፤- የአቶ የሺዋስ ፓርቲ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበትን ፌደራላዊ ስርአት አፍርሼ፤ በወንዝና በተራራ በመሸንሸን የአንድ ብሄራዊ ማንነትን የበላይነትን በመጫን አሃዳዊ ስርአት እመሰርታለሁ ብለው ምርጫ ላይ መቅረብ ይችላሉ። አሁን እያደረጉ እንዳሉት ማለት ነው። በዚህ አቋማቸው የኢትዮጵያ ሶማሌ፤ የአፋር፤ የጋምቤላ፤ የቤኒሻንጉል፤ የኦሮሞ፤ የሃረሪ፤ የሲዳማ፤ የወላይታ፤. . . ህዝብን ድጋፍ ኖሯቸው አብላጫ ድምጽ ካገኙም ስልጣን በውክልና መረከብ ይችላሉ። የፖሊሲ ለውጥ ለማምጣት ስርአት በሃይል መለወጥ የግድ የሚል አንዳችም ምድራዊ ምክንያት የለም።

በአጠቃላይ፤ ባለፈው ዓመት በአገሪቱ ተቀስቅሶ የነበረው ሁከት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮቹ እንዳሉት ሰላማዊ አልነበረም። ህዝቡ የፖሊሲና የስርአት ለውጥ ጥያቄም አላቀረበም። ህገመንግስታዊ ስርአቱ ህዝብ የፖሊሲና የስርአት ለውጥ ፍለጋ የሃይል ተቃውሞ ውስጥ እንዲገባ የሚያስገድድ አይደለም። እናም የፓርቲዎቹ አመራሮች ባለፈው ሳምንት "አይደገምም" ብለው በተሃድሶ ነጻ የተለቀቁትን ዜጎች ጉዳይ መነሻ በማድረግ የሰጡት አስተያየት ከእውነታው የራቀ፤ እንዲያውም አራምባና ቆቦ ነው!